## ሐሰተኛ ዕፅን የሚመለከቱ እውነታዎች

- ዲሲ ውስጥ የሐሰተኛ ዕፅ ተጠቃሚዎች አማካይ ዕድሜ 13 ዓመት ነው፡፡
- በዲሲ ውስጥ ከሚኖሩ አስር ወጣቶች መካከል አንዱ በ 2011 ሲንቴቲክ ማሪዋና ወይም ሐሰተኛ ዕፅ የተጠቀመ መሆኑን የዲሲ የወጣቶች ስጋት ባህርይ ጥናት 2013 ያመለክታል፡፡
- በአሁኑ ጊዜ ሐሰተኛ ዕፅ ከማሪዋና ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ዘንድ ጥቅም ላይ የሚውል ሕገ ወጥ ዕፅ ነው፡፡

## የተጠቃሚ ምልክቶች

**ታዳጊ ልጅዎ ሐሰተኛ ዕፅ ተተቃሚ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ከሚረዱዎ ምልክቶች መካከል፡**

- ”ዕጣን” ወይም “ባለ ጥሩ ሽታ ዕፅዋት” የሚል ምልክት የተለጠፈባቸውና የካርቶን ጽሁፎች ዌም ሌሎች የሚታወቁ አርማዎች ያሉባቸው አነስተኛ እሽጎች፡፡
- ከባድ የቅርንፉድ ሽታ
- ፒፓዎች፣ ጥቅል ወረቀቶች፣ ስክሪኖች፣ ላይተሮች/ክብሪትና ሌሎች ለዕፅ አጠቃቀም የሚውሉ ዕቃዎች መኖራቸውን ያጣሩ፡፡

**የዕፁ ተጠቃሚ የሚያሳያቸው አካላዊ ምልክቶች፡**

- **የመቅበጥበጥ ስሜት**
- **ከፍ ያለ የደም ግፊት፣ የልብ ምትና ፈጣን የልብ ምት**
- **ራስን አለመቆጣጠር**
- **የቆዳ መገርጣት**
- **ከፍተኛ ላብ መውጣት**
- **የሰውነት አለመታዘዝ**
- **ማስታወክ**

የሐሰተኛ ዕፅ አካላዊ ተጽእኖዎች በፍጥነት ሊጎለብቱ ሲሆን ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ ውስጥ ብቻ ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ምልክቶቹ ከአንድ እስከ ስምንት ሰዓት ሊቆዩ ይችላሉ፡፡



## ስለ ሐሰተኛ ዕፅ ከታዳጊ ልጅዎ ጋር ይነጋገሩ

ከታዳጊ ልጅዎ ጋር ሐሰተኛ ዕፅን በተመለከተ መወያየቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ታዳጊ ልጅዎ ሐሰተኛ ዕፅ በት/ቤት፣ ከጓደኞቹ ጋር ሲዝናና ወይም በፓርቲዎች ላይ ሊያጋጥመው ይችላል፡፡ ወይም ሐሰተኛ ዕፅ የሚጠቀም ሰው ሊያውቅ ይችላል፡፡ የሐሰተኛ ዕፅን አደገኛነት በተመለከተ መረጃ ለመለዋወጥ ከታዳጊ ልጅዎ ጋር ጥቂት ጊዜ ያሳልፉ፡፡

**ከታዳጊ ልጅዎ ጋር በሚወያዩበት ወቅት ሊጠቀሟቸው ከሚችሉ ዋነኛ መልእክቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡**

- **ጤናማና ደስተኛ እንደትሆን እፈልጋለሁ፡፡**
- **ስሜቶችህን ወይም ባህርይህን የሚቀይር ማንኛውም ነገር ማጨስ፣ መጠጣት፣ መብላት ወይም በመርፌ መወጋት አደገኛ ነው፡፡**
- **ዕፅ መጠቀም - አወሳሰዱ ምንም ዓይነት ቢሆን - የተዛባና ጤናማ ያልሆነ ውሳኔ ለመወሰን ይገፋፋል፡፡**
- **ሐሰተኛ ዕፅ ተጨባጭ የሆኑ አደገኛ ተጓዳኝ ውጤቶች ያሉት ዕፅ ነው፡፡**
- **እንደማንኛውም ዕፅ ሁሉ፣ በሐሰተኛ ዕፅ ውስጥ ስላለው ነገርም ሆነ አንተ ላይ ስለሚስከትለው ተጽእኖ ለማወቅ አይቻልም፡፡**

ሐሰተኛ ዕፅን በተመለከተ ተጨማሪ
መረጃ ለማግኘት ቀጣዩን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡

**www.K2ZombieDC.com**

የወላጅ መምሪያ፡

# K2 ZOMBIE DC

DANGER: FAKE WEED + U = ZOMBIE



## ልጆችዎ ከእርስዎ የሚደብቁት ነገር ምንድን ነው?

**www.K2ZombieDC.com**

# K2/ZOMBIE DC

DANGER: FAKE WEED + U = ZOMBIE

የዲሲ የባህርያዊ ጤና መምሪያ የሀሰተኛ ዕፅ አጠቃቀም በተለይ በወጣቶች ዘንድ የከፋ እየሆነ መምጣቱን ተገንዝቧል፡፡ በተጨማሪም፣ ሐሰተኛ ዕፅ ለወጣቶች በቀጥታ የሚሸጥበት ሁኔታ አለ፡፡

ሐሰተኛ ዕፅ የሚያስከትላቸው ዘላቂ የጤና ችግሮች እስካሁን ሙሉ በሙሉ ያልታወቁ ቢሆንም፣ የአጭር ጊዜ ውጤቶቻቸው ግን እጅግ ጎጂ - ለሞት የሚያበቁ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ እነዚህን ዕፆች ከወጣቶች ማራቅ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

**ይፈልጉት!!!**

---

**አውነታውን ይወቁሰ**

**www.K2ZombieDC.com**

## ሐሰተኛ ዕፅ ምንድን ነው?

ሐሰተኛ ዕፅ ማለት የቅጠላ ቅጠል ውህድ ሆኖ በውስጡም ደረቅና ቁርጥራጭ ተክል እንደዚሁም ጉዳት አምጪ የኬሚካል ጭማሪዎችን የያዘና ለወጣቶች በቀጥታ ሽያጭ ላይ የሚውል ሲሆን አስተሻሸጉም ሶስት ፖውንድ በሚመዝን የፕላስቲክ ከረጢት ውስጥ ነው፡፡ የፕላስቲክ ከረጢቱ በሚያምር ዲዛይን የተጌጠ ሲሆን በላዩም ላይ የካርቱን ምስሎች ወይም የሚታወቁ አርማዎች አሉበት፡፡ ሐሰተኛ ዕፅ በሲጋራ፣ በመጠጥ ወይም በምግብ መልክ በሚውዱት ሰዎች ላይ እጅግ በጣም የከፋ ጉዳት ያስከትላል፡፡

በሐሰተኛ ዕፅ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ሲንቴቲክ ኬሚካሎች የሚያስከትሉት ጉዳት ሙሉ ዝርዝር እስካሁን አልተረጋገጠም፡፡ በእነዚህ ዕፆች ውስጥ ኬሚካሎች ጥቅም ላይ መዋላቸው ለአንድ ጊዜ ብቻ እንኳን ብንጠቀመው ለሞት የሚያደርስ ጉዳት ያስከትላል ማለት ነው፡፡

## ሐሰተኛ ዕፅ በህዝብ ጤና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት

የሐሰተኛ ዕፅ ተጠቃሚዎች ከማሪዋና ተጠቃሚዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ስሜት የሚሰማቸው ይሆናል፤ ነገር ግን ይህ ሲንቴቲክ ዕፅ በውስጡ ጎጂ ኬሚካሎችን የያዘ በመሆኑ ተጠቃሚዎች ሳይኮቲክና ነጌቲቭ የጤና ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል፡፡ ሐሰተኛ ዕፅ የሚያስከትላቸው የጤና እና ስነ-ልቡናዊ ጉዳቶች ገና እስካሁን አልታወቁም፡፡ ስለሆነም፣ ጤና ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ምን ያህል የከፋ እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡

ሐሰተኛ ዕፅ ከሚያስከትላቸው የስነ-አእምሮ ጤና ችግሮች መካከል ከፍተኛ ፍርሃት፣ ሁሉንም ሰው የመጥላት በሽታ፣ የመሸበር ሁኔታ፣ ራስን ማግለል/ከሌሎች መነጠል፣ ስነ-አእምሯዊ ቅዠቶችና የሌለ ነገርን ማሰብ የመሳሰሉት ናቸው፡፤ ዕፁን መተቀም የድብታ ሕመም፣ የፍርሃትና የስጋት ስሜት እንደዚሁም የመሸበር ሁኔታ የመሳሰሉ ዘላቂ የአእምሮ በሽታዎችን ሊያስከትል ይችላል፡፡ የስነ-አእምሯዊው ባህርይ የ"ዞምቢ" ተጽእኖ ተብሎ ይጠራል፡፡

በሐሰተኛ ዕፅ ውስጥ ያሉት ጎጂ ኬሚካሎች የልብ ምት መፍጠን፣ ማስታወክ፣ ሰውነት መቆጣት፣ ግራ መጋባት፣ የሰውነት መንቀጥቀጥ ወይም የሰውነት አለመታዘዝና በሌለ ነገር ውስጥ በሃሳብ መዋለል ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ችግሮች የዕፁን ተጠቃሚዎች ብዙውን ጊዜ ወደ ድንገተኛ የሕክምና ክፍል እንዲገቡ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ሐሰተኛ ዕፅ ከአንጎል መጎዳት፣ ከልብ ድካምና ከኩላሊት በሽታ ጋር ይያያዛል፡፡ እንደዚሁም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከሞትም ጋር ይያያዛል፡፡




